# <u>የመሪ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸው</u>

መሪ በአገልግሎቱ ውስጥ የተለያዩ ተግዳሮቶች ይገጥመዋል። አገልግሎት ዋጋ የሚያስከፍል ከመሆኑ የተነሳ በመስዋዕትነት የሚደረግ ነው። ይህንን ለማረጋገጥ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመስዋዕትነት ያገለገሉ አገልጋዮችን ማየት በቂ ነው። ከእነዚህም ውስጥ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ኤልያስ፣ ኤርምስ፣ ጳውሎስና የአገልግሎት ሞዴል የሚሆንልን ኢየሱስ ክርስቶስ ይገኙበታል። እነዚህ አገልጋዮች በብዙ ተግዳሮት ውስጥ በማለፍ በድል ተልዕኮአቸውን ፈጽመው ያለፉ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ በተግዳሮት ተሰናክለው ከተጠሩበት ዓላማ በመውጣት ለውድቀት የተዳረጉ ደግሞ ብዙ መሪዎች በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተጠቅሰዋል። በጥቅሉ ስንመለከተው የመሪ ተግዳሮቶች እጅግ ብዙ ናቸው። ይሁን እንጂ እኔ በዚህ ጊዜ ቅድሚያ ልሰጠውና ላተኩር የምፈልገው በዘመናችን ለመሪዎች ተግዳሮት ናቸው የምላቸው ነጥቦች ላይ ነው። ከዚህም ጋር በማያያዝ የመሪ ተግዳሮትን በድል በማለፍ ከውድቀት ማምለጥ የምንችልባቸውን መፍትሔዎች ለማቅረብ እሞክራለሁ።

ለመሆኑ በዘመናችን ለመሪዎች እንቅፋት የሚሆኑና ከተጠሩበት ዓላማ የሚያሰናክሉአቸው ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

1. <u>እንደ መሪ የደቀ መዝሙርነትን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆን።</u>

ሁላችንም እንደምናውቀው ከአገልግሎት ጥሪ በፊት ቀድሞ የደረሰን የድነት ጥሪ ነው። አገልግሎት ደግሞ እንደ ጥሪያችን በመኖር የሚከናወን እንጂ ሞያተኝነት አይደለም። ስለዚህ ስናገለግል የደቀመዝሙርነት ሕይወትን እየኖርን መሆን አለበት። ይህን ሕይወት መኖር ደግሞ መስቀልን መሸከም የሚጠይቅ ነው። ማንኛውም ስለ ክርስቶስና ስለ ስራው ብለን የምንቀበለው መከራና ችግር ሁሉ የእኛ መስቀል ነው። መስቀላችንን መሸከምና አገልግሎት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

> ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም። (ሉቃስ 14፡27)

ይህ ማለት ኢየሱስ በየትኛውም አቅጣጫ ትክክል እንደሆነ በማሰብ በሁኔታዎች ሁሉ እርሱን እስከ ሞት ድረስ መከተል ነው። ብዙ ጊዜ የዘመኑ መሪዎች ነን የምንል ስለ ክርስቶስ ልንሰደብ፣ ልንናቅ፣ ወዘተ አንፈልግም። ይልቁንም ስማችንን ለማግነንና ለማሳወቅ የክርስቶስን ስም እስከ መሸፈን እንደርሳለን።

> ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል። (ሉቃ 6፡40)

ለመሆኑ እኛ መሪዎች ክርስቶስን እንመስላለን?

## 2. የአገልግሎትን ዋነኛ ዓላማ መዘንጋት፡፡

እግዚአብሔር መሪዎችን ሲጠራ ዋነኛ ተልዕኮአቸው ሰዎችን በክርስቶስ ፍጹም አድርገው በመስራት ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከኢየሱስ እና ከጳውሎስ ንግግር መረዳት ይቻላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋና ደም ተካፍሎ ለሰዎች ሕይወት ያውም የተትረፈረፈ ሕይወት ለመስጠት እንደመጣ ራሱ ግልጽ አድርጓል፡፡ የኢየሱስ ቅድሚያ ሰዎች እንጂ ፕሮግራሞች አይደሉም፡፡ ፕሮግራም ያካሂድ የነበረው ሰዎች የተትረፈረፈ ሕይወትን እንዲለማመዱ ነው፡፡

ኢየሱስ በስጋና ደም በመካፈል ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዓላማ በእርሱ ተዋጅተው፣ እርሱ የሚሰጠውን የተትረፈረፈ ሕይወት የተለማመዱና እርሱን የሚመስሉ ሰዎች ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነበር፡፡ ለዚህ ነው እንዲህ በማለት የተናገረው፡-

> ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ፡፡ (ዮሐ 10፡፡10)

ጳውሎስ የሚታወቅበት አንዱ ባህርዩ ሲያገለግል በሰዎች ላይ ያነጣጠረና ሰው ተኮር የሆነ አገልጋይ መሆኑ ነበር፡፡ ወንጌል ቢሰብክ፣ ቢያስተምር ሌሎችንም ተግባሮች ቢፈጽም ይህንን ሁሉ የሚያደርገው ክርስቶስን የሚመስሉ ሰዎችን በመስራት ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ነው፡፡ ሰዎች ከመንፈሳዊ፣ ስጋዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ እስራት በመፈታት እግዚአብሔርን እያከበሩ እንዲኖሩ ለመርዳት ነበር፡፡ ለጳውሎስ መስበክና ማስተማር በራሱ ግብ አልነበረም፡፡ ይልቁንም የሚያከናውናቸው ተግባሮች ዓላማውን/ግቡን ለመጨበጥ የሚጠቀምበት መንገድ (means) ነበር፡፡

> እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ (ቁ. 28ሀ)

- *ታዲያ እንደ መሪዎች ራሳችንን ስንመዝነው አገልግሎታችን ሰው ተኮርና ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን በሕይወታቸው እንዲገነቡ የሚያግዝ ነው?*

## 3. የነጠረውን የእግዚአብሔርን ቃል ከመስበክና ከማስተማር ይልቅ ቃሉን መቀላቀልና መሸቃቀጥ፡፡

ዛሬ ብዙ ሰዎች ቃሉን ከመስበክ ይልቅ ብዙ የግል ገድልና ዲስኩር በየመድረኩ የሚያሰሙበት ዘመን ነው፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ዋነኛ የአገልግሎታችንን ተልዕኮ በመዘንጋት ያለ አግባብ የሚገኝን ጥቅም በማሳደድ (2 ጢሞ 3፡9) የእግዚአብሔርን ቃል የሚሸቃቅጡ አሉ፡፡ ከዚህ የተነሳ ስር የሰደዱና ክርስቶስን የሚመስሉ ሰዎች ከመስራትና ከማፍራት ይልቅ ግልብና ጥልቅ ያልሆነ ሕይወት ያላቸውን ሰዎች እየሰበሰብን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰው የማቅረቡን ዓላማ የዘነጋ እንደዚሁም ተልዕኮአችንን የሚያደበዝዝና እጅግ የሚጎዳ ነው፡፡

የአገልግሎታቸው ዓላማ ክርስቶስን የሚመስሉ ሰዎች ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንደሆነ የገባቸው አማኞች ግን እንደዚህ አይደሉም። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ተናገረ፦

> የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት እንደ ብዙዎቹ አይደለንምና፤ በቅንነት ግን ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን። (2 ቆሮ 2፡17)

ጳውሎስ ዓላማውን ለመጨበጥ ወይም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰው ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ይጠቀምበት የነበረው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነበር። ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ ክርስቶስን የሚመስል ሰው መስራት አይቻልም። በመለኮት መልክ ሊገለጥ የተገባውን ሰው እስትንፋሰ-መለኮት ባለው በእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ በስተቀር በምንም መንገድ መስራት አይቻልም።

> ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን (ቁ. 28ለ)

ለዚህ ነው ኢየሱስና ጳውሎስ የሚከተሉትን መመርያዎች በግልጽ የሰጡንና ያስተማሩን።

> ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ። (ማቴ 28፡20)

> የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። (ቆላስይስ 3፡16)

4. <u>ኢየሱስን ከመስበክ ይልቅ ራስን መስበክ።</u>
   እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤ ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥ (1 ቆሮ 1፡23)

ከዚህ የጳውሎስ ንግግር ስንመለከት ዋነኛው እግዚአብሔር የሰጠን ተልዕኮ ክርስቶስን በምንኖረው ሕይወትና በቃላችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንሰብክ ነው። ለሰዎች ሁሉ ልናስተዋውቀውና ልንገልጠው የሚገባ ከኢየሱስ ክርስቶስ በላይ የላቀ ማንም የለም። እውነቱ እንዲህ ሆኖ ሳለ ከላይ እንደጠቀስኩት ዛሬ ሰዎች ከክርስቶስ ይልቅ የራሳቸውን ገድልና ማንነት በማውራት ክርስቶስን ሳይሆን ራሳቸውን የሚሰብኩ ብዙዎች ናቸው። የጳውሎስ የስብከቱ ጭብጥ ግን የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

> የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ። (2 ጴጥ 1፡16)

ሰዎች እንዲያውቁት የምንፈልገው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ምክንያቱም ሰዎች ክርስቶስን የሚመስሉት ወይም በክርስቶስ ፍጹም ሆነው የሚሰሩት የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነው ክርስቶስን ማየት ሲችሉ ነው። ይህ ደግሞ የሚሆነው በአገልግሎታችን ክርስቶስን መግለጥ ስንችል ነው።

> ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ። (ቆላ 2፡2)

የጳውሎስና የሌሎቹም ሐዋርያት አገልግሎት ሰዎች ክርስቶስን እንዲያዩና እንዲመለከቱ ማድረግ ነበር። ስለዚህ በማንኛውም መንገድ ማለትም በሕይወታችንም ይሁን በቃላችን ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት እንዲችሉ ልንረዳቸው ይገባናል።

> ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤ (ዕብ 3፡1)

ለሰዎች ከክርስቶስ ይልቅ ራሳችንንና ሌሎች ሕይወት የማይሆኑ የገዘፉ የሚመስሉ ነገሮችን ስናሳያቸው ከሕይወት ይልቅ አዚም እንለቅባቸዋለን። ዓይናቸውን ከክርስቶስ በማንሳት ለማይረባ ፍልስፍና ታልፈው ይሰጣሉ።

> የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው? (ገላ 3፡1)

- ታዲያ የእኛስ ሕይወትና ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ፤ እርሱን የሚገልጥና የሚያጎላ ነውን?

**ለ) <u>በአገልግሎት ሂደት ለብቸኝነት ልንዳረግ ስለምንችል።</u>**

እግዚአብሔር ብዙ የተጠቀመባቸው ሰዎች አንድ ወቅት ላይ ብቸኝነት ሊሰማቸው፣ተስፋ ሊቆርጡና እጅ ለመስጠት ሊዳዳቸው ይችላል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኤልያስ ነው።

> እርሱም አንድ ቀን የሚያህል መንገድ በምድረ በዳ ሄደ መጥቶም ከክትክታ ዛፍ በታች ተቀመጠና። ይበቃኛል አሁንም፥ አቤቱ፥ እኔ ከአባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰድ ብሎ እንዲሞት ለመነ። ... እርሱም፦ ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ ነፍሴንም ሊወስዱአት ይሻሉ አለ። (1 ነገስት 19፡4፣10)

ምንም እንኳ እግዚአብሔር እጅግ ታላላቅ የሆኑ ስራዎችን ለመስራት ኤልያስን ቢጠቀምበትም ከላይ ካለው ጥቅስ እንደምናየው ተስፋ በመቁረጥ ከኤልዛቤል ዛቻ ሕይወቱን ለማትረፍ ሲሸሽ እንመለከታለን። ከዚህ የተነሳ እጅ ለመስጠት ተቃርቦ እናገኘዋለን። እኛም እንዲህ ዓይነት ብቸኝነትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሊሰማን ስለሚችል በመስዋዕትነት ለማገልገል ልንጨክን ይገባናል።

**ሐ) <u>በአገልግሎት ሂደት የሰዎች ነቀፋና የጠላት ትግል ሊገጥመን ስለሚችል።</u>**

የአገልጋዮች የእያንዳንዱ እንቅስቃሴ በሰዎች እይታ ውስጥ ከመሆኑ የተነሳ ትንሹ ጥፋታቸውም እንደ ትልቅ ሊቆጠር ይችላል። ይህ ተግዳሮት በመጽሐፍ ቅዱስ በመሪነት ትልቅ ስፍራ የነበራቸው ሰዎችም ጭምር ገጥሞአቸዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ደግሞ ሙሴ ነው።

> ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ። እርሱም፦ በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሮአልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ እግዚአብሔርም ሰማ። (ዘኁ 12፡1-2)

ስለዚህ በአገልግሎት ሂደት የሰዎች ነቀፋና የጠላት ትግል ሲገጥመን እግዚአብሔር የሰጠንን ጥሪና ተልዕኮ በመረዳት እንደዚሁም በሁኔታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደሚሆን የሰጠንን ተስፋ በማሰብ በጽናት አገልግሎታችንን ዳር በማድረስ እግዚአብሔር የሰጠንን አደራ በውጤታማነት ልንፈጽመው ይገባናል።

**መ) በአገልግሎት ሂደት ዝለትና ድካም ሊገጥመን ስለሚችል።**

ብዙ አገልጋዮች በአገልግሎት ሂደት ዝለትና ድካም ገጥሞአቸዋል። ለዚህም ሙሴ ጥሩ ምሳ ሊሆነን ይችላል።

> ሙሴም እግዚአብሔርን አለው፡- ለምን በባሪያህ ላይ ክፉ አደረግህ? ለምንስ በፊትህ ሞገስ አላገኘሁም? ለምንስ የዚህን ሕዝብ ሁሉ ሸክም በእኔ ላይ አደረግህ? አንተ ለአባቶቻቸው ወደ ማልህላቸው ምድር አደርሳቸው ዘንድ። ሞግዚት የሚጠባውን ልጅ እንድታቅፍ በብብትህ እቀፋቸው የምትለኝ፥ በውኑ ይህን ሕዝብ ሁሉ እኔ ፀነስሁትን? ወለድሁትንስ? በፊቴ ያለቅሳሉና።

የምንበላውን ሥጋ ስጠን ይላሉና ለዚህ ሕዝብ ሁሉ የምሰጠው ሥጋ ከወዴት እወስዳለሁ? እጅግ ከብዶኛልና ይህን ሁሉ ሕዝብ ልሸከም አልችልም። እንዲህስ ከምታደርግብኝ፥ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፥ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ፥ እባክህ፥ ፈጽሞ ግደለኝ። (ዘኍ 11፡11-15)

መሪዎች ከሚመሩት ሕዝብና አብረዋቸው ከሚያገለግሉአቸው ሰዎች በሚደርስባቸው የተለያየ ግፊት ልባቸው ይዝላል። እንዲህ ዓይነቱ የመሪነት ፈተና ሲደርስብን ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ልብን ማፍሰስና ምሪትን ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

**ሠ) <u>በአገልግሎት ሂደት ጫናና ግራ መጋባት ሊገጥመን ስለሚችል።</u>**

ሙሴ ከአገልግሎት ጫና የተነሳ እግዚአብሔርን ብትገድለኝ ይሻለኛል በማለት ለምኗል። ይህ እውነት ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በግልጽ መረዳት ይቻላል።

እንዲህስ ከምታደርግብኝ፥ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ፥ በእኔ ላይ የሚሆነውን መከራ እንዳላይ፥ እባክህ፥ ፈጽሞ ግደለኝ። (ዘኍ 11፡14-15)
አሁንም፥ አቤቱ፥ ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው። ... ፀሐይም በወጣች ጊዜ እግዚአብሔር ትኩስ የምሥራቅ ነፋስ አዘጋጀ ዮናስ እስኪዝል ድረስም ፀሐይ ራሱን መታው ለራሱም ሞትን ፈለገና። ከሕይወት ሞት ይሻለኛል አለ። (ዮናስ 4፡3፣8)

## 5. <u>እንዴት መታደስ ይቻላል</u>

**ሀ) እግዚአብሔር በአጠገባችን ቆሞ ሲያበረታን።**

ዳሩ ግን የስብከቱ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ። (2 ጢሞ 4፡17)

**ለ) የቀበልነውን ራዕይና ጥሪያችንን በማሰብ መታደስ ይቻላል።**

ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ (**ሽልማት ለማግኘት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ**)። (ፊል 3፡13-14)

**ሐ) በሕብረት (በቡድን) አብረን በመስራት መታደስ ይቻላል።**

ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው። ከራስ እስከ ጢም እንደሚፈስስ፥ እስከ አሮን ጢም፥ በልብሱ መደረቢያ እንደሚወርድ ሽቱ ነው። በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ እንደ አርሞንዔም ጠል

ነው በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና። (መዝ 133፡1-3)

**መ) ክህሎታችን ሲታደስ (ልቀት ሲገለጥብን) እኛም እንታደሳለን።**

እናንተም በሁሉ ነገር ይኃውም በእምነት፣ በቃል፣ በዕውቀት፣ በፍጹም ትጋትና ለእኛም ባላችሁ ፍቅር ልቃችሁ እንደተገኛችሁ፣ በዚህም የቸርነት ስራ ልቃችሁ እንድትገኙ አደራ እንላችኋለን። (2 ቆሮ 8፡7)

**ሠ) በማረፍ (እረፍት በመውሰድ) መታደስ ይቻላል።**

እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። (ዘፍ 2፡2)

**ረ) ሰዎች አገልግሎታችንን በመገንዘብ እንክብካቤ ሲያደርጉልን እንታደሳለን።**

ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛልና ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው። (2 ጢሞ 4፡11)

ከተገረዙት ወገን ያሉት፥ አብሮ ከእኔ ጋር የታሰረ አርስጥሮኮስ የበርናባስም የወንድሙ ልጅ ማርቆስ ኢዮስጦስም የተባለ ኢያሱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። ስለ ማርቆስ። ወደ እናንተ ቢመጣ፥ ተቀበሉት የሚል ትእዛዝ ተቀበላችሁ። በእግዚአብሔር መንግሥት ከእኔ ጋር አብረው የሚሠሩት እነዚህ ብቻ ናቸው፥ እኔንም አጽናንተውኛል። (ቆላ 4፡10-11)

**ማጠቃለያ**

ስለዚህ መሪዎች የእግዚብሔርን ሕዝብ ሲመሩ በተለያዩ መንገዶች ተግዳሮት ሊገጥማቸው እንደሚችል ማወቅ ይገባቸዋል። ይህንን አስቀድሞ በመረዳት ጠላት ልባቸውን በማዛል እጅ እንዲሰጡና አገልግሎታቸውን ዳር ሳያደርሱ እንዲያቆሙ የሚያደርገውን ጥረት ማስቆም መቻል አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ከላይ የተመለከትናቸውን መፍትሔዎች መከተሉ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር በዘመናት መካከል ለባሪያዎቹና ለአገልጋዮቹ የሰጠውን የተስፋ ቃል እያሰቡ ማገልገል ወሳኝነት አለው። ይህ የተስፋ ቃል በሁኔታዎች ሁሉ ስናልፍ ጸንተን ለመቆም ጉልበት ይሆነናል።

> በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደ ሆንሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም፥ አልተውህም። (ኢያሱ 1፡5)
>
> አሁንም ያዕቆብ ሆይ፥ የፈጠረህ፥ እስራኤልም ሆይ፥ የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ በስምህም ጠርቼሃለሁ፥ አንተ የእኔ ነህ። በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፥ ነበልባሉም አይፈጅህም። (ኢሳይያስ 43፡1-2)